


## ማን ነው ሽብርተኛው?

# እስክንድር ነጋ ወይስ የወያኔው መንጋ!

ከቴድሮስ ሐይሌ (tadyha@gmail.com)

In human history, terrorism is widely recognized as the world most famous enemy of mankind. As history itself will admit that terrorism is annihilation with far-reaching and destructive effects, it is the cruelest of crimes against humanity.

በታላቋ ሃገራችን ቅድስቲቱ ኢትዮጵያ ላለፉት 20 አመታት የተንሰራፋው ሠይጣናዊው ሽብርተኛውና ዘረኛው የትግራይ ነፃ አውጭ ነኝ ባዩ መልቲ የማፍያ ቡድን ጠባብ አላማውን ለማሳካት ፍቅርን በሰበኩ ፤ አንድነትን በመከሩ ፤ስለ እኩልነት በተናገሩ የዲሞክራሲ ታጋዮችና ፤ ሠላማዊ ዜጎች ላይ ማለቂያ የሌለው ስም በመለጠፍ በእንበለ ፍርድ በየአደባባዩ የረሸናቸው በየእስር ቤቱ ያጎራቸው ዜጎች ቁጥር ለመጥቀስ እስኪያዳግት ድረስ በግፍ ላይ ግፍ በበደል ላይ በደል ከመፈጸም ሊታቀብ ይቅርና ጭራሽ እየባሰበት ከመሄድ ሊገታው የሚችል ሁኔታ ባለመፈጠሩ የጭቆና የብረት ቀንበሩን በሕዝብ ላይ በመጫን ሃገሪቱን በፍጥነት ወደ ታላቅ እስር ቤትነት ለውጧታል ።

የሕወሃት ሠይጣናዊ ቡድን በአሁኑ ወቅት በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብዮት ወጋገን ለሃገራችን ጭቁን ሕዝብ አበረታችና አርአያ ሆኖ ከስሩ እንዳይመነግለው ከፉኛ ከመስጋቱ የተነሳ ለአለም መሣቂያ እስኪሆን ድረስ በሠላማዊ እንቅስቃሴያቸው ፤ በአስተሳሰብ አድማሳቸው በምሁራዊና ፤ በስነምግባራዊ ተክለሠውነታቸው በሃገር ውስጥም ሆነ በዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ጭምር አክብሮት የተቸራቸውንና እውቅና ያላቸውን ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን አበው "የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ " እንዲሉ አሸባሪ ብሎ በመፈረጅ የጀመረው የዚህ ሰሞኑ የእስር ዘመቻ በሚሊዮን በሚቆጠር ሠራዊትና ነጭለባሽ የሚጠበቁት የአገዛዙ መሪዎች ብዕር ባነገቡ ንፁሐን

## የወያኔ

የዲሞክራሲ ተሟጋቾች መርበድበዳቸውና ጥቂቶችን በማሰር አይቀሬውን ህዝባዊ አመጽ ለመቀልበስ የመሞከራቸው ሂደት የአረመኔ አገዛዛቸውን መቀበሪያ ጉድጓድ ከማራቅ ውጭ ከቶም ሊያስቀሩት የማይችሉት የቁጣ ማዕበል ሞገዱ ተነስቶ ሳይጠራርጋቸው ከሰጠሙበት ድቅድቅ ዘረኛና ኋላቀር የጥፋት ጨለማ ወጥተው ራሳቸውንም ሆነ ሃገሪቱን ከመከራ ለመታደግ መልካም እድል ቢጠቀሙበት በእጃቸው ይገኛል ።(ጋዳፊን ያየ በሕዝብ አይቀልድም )

የሕወሐት መሪዎች አረመኔያዊ ተግባር በተሟላ መረጃ በአለም አቀፍ የሰብዐዊ መብት ተቋማትና በምዕራቡ መንግስታት የሚታወቅና መሪውን ጨምሮ በተወሰኑትም ላይ በሰው ዘር ፍጅት(GENOCIDE) ክስ የቀረበባቸው መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም! ከጋንቤላ እስከ አዋሳ ፤ ከአሰቦት እስከ ጅጅጋ ከአቢአዲ እስከ አደባባይ እየሱስ ፤ እንዘርዝረው ቢባል ብዕርና ወረቀት የሚበቃው አይመስለኝም 17 አመት በትግል ስም 20 አመት በመንግስትነት ጥብቆ በተከተለው የሽብር አገዛዝ  የስንት ንፁሐን ዜጎች ደም በከንቱ ፈሰሰ በምርጫ 97 የሕዝብ ድምጽ መነጠቁ ሳያንስ ከሕጻን እስከ አረጋውያን የተካሄደው ሽብራዊና ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ከቶም የሚዘነጋ አይደለም እዚህ ላይ አንድ የትግል ጓዳችን ቤተሰብ ላይ የተፈጸመውን የሕወሀትን አረመኔ ድርጊት ለማስታወስ እገደዳለሁ።

የመኢአድ/ቅንጅት የወጣቶች ም/ቤት አባል በነበረችው ጠንካራዋ ታጋይ ወጣት አለምዙረያ ተሾመና አባቷ የአዲስ አበባ ክልል ም/ቤት ተወዳዳሪ የነበሩት አቶ ተሾመ በነበረው ሕጋዊ የምርጫ ሂደት



ቅንጅትን ወክለው በማሸነፋቸውና የሕዝብን ድምጽ እንዲከበር በመጠየቃቸው ብቻ እኚህን ጨዋና በስነምግባራቸው በሁላችን ዘንድ አክብሮት የተቸራቸውን የሰላምና የዲሞክራሲ ታጋይ ከቤታቸው አፍኖ ሊወስዳቸው የመጣውን የሕወሐት አረመኔ ወታደሮች የአቶ ተሾመ ባለቤትና ሕጻናት ልጆቻቸው በልመናና ተማጽኖ የአባወራው ታስሮ መሄድ በመጠየቃቸው ብቻ እኚህን ምንም የማያውቁ ግሳጼ እንኳን የሚበዛባቸውን ምስኪን የህጻናት እናት የአጋዚው ታጋይ በያዘው ክላሽ ደጋግሞ በመተኮስ ሴትዮይቱን አፍ ባልፈቱ ሕጻናት ልጆቻቸው ፊት ገድለው እናቴን ብሎ ትንሽ ነብስ ያወቀው ተዳጊ በመጮሁ እሱን ደግሞ እግሩን ተኩሶ በማቁሰል የውጭ ወራሪ ጠላት እንደገደሉ ምስኪኑን ቀን የጨለመባቸውን አቶ ተሾመን ወደ እስር ቤት ይዘው ሄዱ።

## የወያኔ

የሕወሐቱ ነብሰ ገዳይ የሽብር ጓድ ባፈሰሰው የንጹህ ሰው ደም የበቀል ዛሩ አልረካምና የሚቿን አስከሬን ለምርመራ በሚል ደግማዊ ምንሊክ ሆስፒታል አስገብቶ የዲሞክራሲና የነፃነት ተጋይ ጓዳችን አለምዙሪያ ተሾመ እናቷን በክብር ለመቅበር የቀረበላት ምርጫ እናቷን የገደላቸው ቅንጅት ነው ብለሽ ፈርሚ የሚል ማስገደጃ ያቀርቡላታል እርሷም በቆራጥነት ራሳችሁ ገላችኋት እንደገና በውሸት እናቴን አልገልም እንደፈለጋችሁ አድርጉት በሚል አቋም ጸንታ ይህንንም ግፍ ለሕዝብ እንዲገለጽ ለሚድያዎች አስተላልፋ ቀሪ ተንከባካቢ የሚያስፈልጋቸውን ሕጻናት ወንድምና እህቶቿን ትታ ሕይወቷን ለማትረፍ እርሳም ለስደት የተዳረገችበት ሁኔታ ከብዙወቻችን የትግል አጋሮቿ ሕሊና የማይጠፋ አሰቃቂ ትዝታ ነው።

ጎበዝ እንግዲህ ኢትዮጵያችን የምትገዛው ዛሬም ይህን በመሠለ ሣጥናዔላዊ ቡድን ነው እናትን ገለው አባትን አስሮ ብላቴናውን አቁስለው ታላቅ እህትን አሰድዶ ቀሪ ሕጻናትን ያለ ተንከባካቢ የትም ሜዳ እንዲበተኑ የሚያደርግ አረመኔው የሕወሐት ቡድን ከአልቃይዳ የማይተናነስ  ጨካኝ ዘረኛና ሽብርተኛ ቡድን መሆኑን ከላይ ከመግቢያ ላይ የቀረበው አለም የተስማማበት የሽብርተኝነት ትርጓሜ በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸም ማናቸውም አይነት የሰቆቃ ተግባር የሚያደርግ ቡድንም ይሁን ግለሰብ ድርጊቱ ፈጻሚውን በሽብርተኝነት የሚየስጠይቅ አድራጎት ነው።

አሮጊት ገዳይ ሕጻን አቁሳይ ቤተሰብ አፍራሽ የሆነው ሠውበላው የመለስ ቡድን እንዲህ ያለ የሽብር ተግባር ፈጻሚና ወንጀለኛ ሆኖ እያለ እንደ እስክንድር ነጋ ያለ የምቾት ሕይወት ያልተጓደለበት እግዚያብሔርን የሚፈራ ሠውን የሚያከብር ለደሀ የሚራራ ለጋስና የዋሕ ንጹህ ሃገሩንና ወገኑን የሚወድ የዲሞክራሲ ፋና ወጊ ደፋርና በሰላማዊ ፖለቲካ ፍጹም የሚያምን ብዙ ግፍ የፈጸመበትን ቡድን እንኳ የማይጠላ የሰላም ሰው እንደሆነ የሚያውቀው ሁሉ የሚመሰክረው ሐቅ ነው እንዲህ አይነቱን መልካም ዜጋ ሽብርተኛ ማለት በሕዝብ መሣለቅና በፍትሕ መቀለድ ነው።

ለማጠቃለል የወያኔ አገዛዝ በሃገር ቤት  በቅርቡ ሐሳባቸውን በነጻነት ባንሸራሸሩት የአንድነትና የመድረክ የፖለቲካ መሪዎችና በጋዜጠኞች ላይ የወሰደው በግፍ የማሰር እርምጃ በመላው የሃገሪቱ ዜጎች ላይ የተቃጣ የእብሪትና አንባገናዊ እርምጃ በመሆኑ በሀገርም ውስጥ ይሁን በውጭ ሃገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዘረና ጎሳ ሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከት ሣይገድበው ያለ ጥፋታቸው  በእስር ለዲሞክራሲ ለፍትሕ የበላይነትና ለሃገር ሉዓላዊነት ሲሉ ለሁላችን የጋራ ጥቅም ሲሉ የታሰሩትን ባስቸኳይ እንዲፈቱ ለማድረግና እንደ ግብጽ ሊብያና ቱንዚያ በሕዝባዊ ንቅናቄ ኋላቀሩንና አሸባሪውን የወያኔ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከጫንቃችን አውርደን ለመገላገል ሁሉም ባለበት በቃ በሚል መንፈስ ወቅቱ የሚጠይቀውን የእናት ሐገር ጥሪ ምላሽ ሊሰጥ ግድ ይለዋል ።  እግዚያብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!!!

የወያኔ